በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ከኤፕሪል 21-30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ እንዲሁም

ከሜይ 1-10 እና ከሜይ 11-20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2025

አዲስ አበባ

1. እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ እና በምስራቅ፣ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በመጨረሻዎቹ አምስት ቀናት የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምዕራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ጥቁር እንበሳ 22.6፣ በአርባምንጭ 19፣ 25.3፣ ድሬ ዳዋ 41፣ ጎዴ 14.4፣ 15.6፣ ጎሬ 40፣ 21፣ 13.4፣ ጅማ 13.4፣ 13.2፣ ነገሌ 14.5፣ አይራ 10.6 ሐሮማያ 11፣ አማን 11.7፣ 10.4፣ አምቦ 35.1 አንገር ጉቲን 12.2፣ አርሲ ሮቤ 10.2፣ አሶሳ 16፣ ቦሬ 38.2፣ 24፣ ቡለን 49.7፣ ቡሬ 30.5፣ 25.5፣ ቡርጂ 28.5፣ ጭራ 35.6፣ 15.3፣12.9፣ 18.7፣ ደምቢ ዶሎ 16.2፣ 15.8፣ 11፣ ዲላ 11.2፣ ዶሎ መና 20.6፣ 10.6፣ 70.3፣ ፊቼ 13.9፣ ፉኙንዶ 20፣28፣ 19.2፣ ጋምቤላ 24.2፣ 40.4፣ ጋቲራ 41.3፣13.2፣ 22.6፣ ጊምቢ 17፣ ቡሌ ሆራ 26.4፣ ሐረር 22.2፣ 19.3፣ ሆሳዕና 17.3፣ እምድብር 25.6፣ ጃራ 30.4፣ ጂንካ 43.5፣ ካቺሴ 23.8፣ ኮንሶ 16፣ 11.7፣ ቁሉምሳ 13፣ ላሬ 12.2፣ 10.2፣13.2፣12፣ ማጂ 12፣ ማንኩሽ 27፣ 31፣ መካነ ሰላም 17.8፣ ሞያሌ 41፣ ሳዉላ 32. 23.4፣ ሰኮሩ 79.2፣ ቴፒ 29.2፣ ተርጫ 17፣ ጽጽቃ 16.4፣ 10.2፣ 31.2፣ ወራቤ 20.6፣ ያቤሎ 14.1፣ የትኖራ 32.4፣ ዶሎ ኦዶ 11.1፣ ግራዋ 10.5፣ ጉበይሬ 22.7፣ ሃመሮ 20.7፣ ካራሚሌ 15፣ ሽላቦ 47.5፣ እንዲሁም ሰቆጣ 13.5 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ19 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-79.2 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ሰኮሩ፣ ዶሎመና፣ ቡለን፣ ሽላቦ፣ ጂንካ፣ ጋቲራ፣ ድሬ ደዋ፣ ሞያሌ፣ ጋምቤላ፣ ጎሬ፣ አማን፣ ቦሬ፣ ጭራ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ
እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



ምስል፡1 ከኤፕሪል 21-30 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ ኮሬ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ ዞኖች ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሀዲያ፣ የሃላባ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ቄልም ወለጋ፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ የደቡብ እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ዶሎ ኦዶ፣ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም እና ዋግህምራ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ የመተከል ዞን፣ ድሬ ደዋና ሐረር ላይ ከ16-110 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ ኮሬ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሀዲያ፣ የሃላባ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቄልም ወለጋ፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ የደቡብ እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ኖጎብ፣ ኤረር፣ ቆራሂ፣ዶሎ ኦዶ፣ ሲቲ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም እና ዋግህምራ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ የመተከል ዞን፣ ድሬ ደዋና ሐረር መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

በሌላ በኩል በመተሃራ፣ በአቦቦ፣ በፉኙዶ፣ በመተማ፣ በገዋኔ፣ በጋምቤላ፣ በሰመራ፣ በአዋሽ አርባ፣ በወሊሶ፤ በጎዴ፣ በፓዌ፣ በድሬ ዳዋ፣ በኑራኤራ፣ በቀበሪዳሀር፣ በአይሻ፣ በሸዋ ሮቢት፣ በጨፋ፣ በጨዋቃ፣ በአዳማ፣ በቻግኒ፣ በቴፒ፣ በአቦምሳ፣ በአሶሳ፣ በሊሙገነት እና በብላቴ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 33.0 እስከ 42.2 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ 4) ፡፡



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1.2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የኤፕሪል የመጨረሻው አስር ቀናት የበልግ አብቃይና ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ቀደም ብለው ከኤፕሪል ወር ጀምሮ ለሚዘሩ የመኸር ወቅት ሰብሎችን ዘር ለመዝራት እና ለማሳ ዝግጅት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ የተገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ እንደነበረዉ ተስተዉሏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የነበረው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በአንዳንድ እርጥበት አጠር በሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን ፈጥሯል (ካርታ 5) ፡፡



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1.3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኤፕሪል ሶስተኛ አስር ቀናት የታችኛው ባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ የታችኛው ስምጥ ሸለቆ እና የመካከለኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች በጣም ከፍተኛ የሆነ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ባሮ አኮቦ፣ ምስራቃዊ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ የመካከለኛው አባይ፣ የላይኛው ተከዜ እንዲሁም በጥቂት የላይኛውና የታችኛው ደቡባዊ አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ የገፀ ምድርንም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብትን ከማሻሻል አንፃር አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የተቀሩት አብዛኛው አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ፣ የታችኛውና የላይኛው አባይ እንዲሁም የታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች ደረቅ ሆነው ቆይተዋል(ካርታ 6)፡፡



ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2 መግቢያ

ሜይ የበልግ ወቅት የመጨረሻ ወር ሲሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት ከደቡብና ከደቡብ ምሥራቅ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሞላ ጎደል ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ዝናቡ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ በመሄድ ብዙ ቦታዎችን ይሸፍናል፡፡ በዚህም መሠረት አብዛኛው የኦሮሚያ ክልልን ጨምሮ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ የሲዳማ ክልል፤የጋምቤላና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ121-260 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ15-20 ቀናት ያህል ያገኛሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይና የአማራ ምዕራባዊ ክፍልና የሱማሌ አካባቢዎች ከ41 እስከ 120 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ለ10 ቀናት ያህል በአማካይ ያገኛሉ። ከበልግ ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በሜይ የመካከለኛው፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች እስከ 30% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።

2.2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሜይ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በመሆኑም በሚቀጥሉት አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና በተለይም የምድር ወገብን በማቋረጥ ወደ ሀገራችን የሚገባው ዕርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፤ በደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡



ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ሜይ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

2.3 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ጨምሮ የደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1-29 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8)፡፡



ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10, የሚኖረወ የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን

ክልል	ዞን	የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን
አሮሚያ	ጅማ፣ ቦረና፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ 30 ሚ.ሜ በላይ)
	አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሌ፣ ባስኬቶ፣ አሪ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ፣ ኤረር፣ ጃራር ዶሎ፣ ፋፈን እና ሲቲ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
አማራ	የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የመካከለኛዉ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
ትግራይ	የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብ ትግራይ፣ የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
አፋር	ጋቢ፣ ሃሪ፣ ማሂ፣ ፋንቲ እና ሃዉሲ ዞኖች	ቀላል መጠን
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ማዕከላዊ ኢትዮጵያ	ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ	ቀላል መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ)
ጋምቤላ	አኙዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ቤንሻንጉል ጉምዝ	ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ሐረሪ		ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)

2.4 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በበልግ ወቅት በመደበኛነት ትኩረት ከሚሹ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል ቀን ላይ የሚኖረው የሙቀት መጠንና ሌሊት ላይ ደግሞ የሚታየው ወበቅ አንዱ ነው። በሜይ የመጀመሪያው አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና በምዕራብ አማራ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት 32 ዲግሪ ሴልሺየስ እንዲሁም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከ35 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 9)።



ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

2.5 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የሜይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሜይ የሁለተኛዉ አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን የሚገባው ዕርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት በደቡባዊው አጋማሽ፣ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 10)፡፡



ካርታ 10 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

1.6 እ.አ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኞዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት እና ቀደም ብለዉ ለተዘሩ ሰብሎች እድገት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በተጨማሪም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩ አልፎ አልፎ በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ የሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት ለወቅቱ የእርሻ ስራ እንቅሥቃሴ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም በተወሰኑ ውሃ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሣዎች ላይ የውሃ መተኛትና የአፈር መታጠብን ሊያስከትል ይችላል። በአጠቃላይ በመጪው በሜይ የመጀመሪያዉ አስር ቀናት የሚኖረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች ለመጠቀም ከታች ያሉትን የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

ዞኖች	የእርጥበት ሁኔታ	አዎንታዊ ተፅዕኖ	አሉታዊ ተፅዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች				
ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የመካከለኛዉ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት	• ለመኸር የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን • የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት • የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር	• የእርጥበት መብዛትን በማይቋቋሙ የአፈር ጠባይ ያላቸው ማሳዎች መጨቀየት እና የውኃ መተኛት • ውሃ ገብ በሆኑና	• የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር እርሻን ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ማከናወን እና ዘር መዝራት • የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን • የውሃ ማንጣፊፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ከወዲሁ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ማዋል

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ		አቅርቦት ለማሻሻል • ለቋሚ ሰብሎች የውኃ ፍላጎት ለማሟላት	በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ	• የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል ያስፈልጋል።
በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች				
ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ የደቡብና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ኤረር፣ ፋፈን እና ሲቲ ዞኖች	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት	• ለበልግ ሰብሎች እድገት • ለመኸር ግብርና እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት • ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል	• የሚኖረው እርጥበት ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን • የደረቅ ሰሞናት መኖር • ከፍተኛ ትነት መኖር	• በተለያዩ ምክንያቶች ዘር ለመዝራት የዘገዩ አካባቢዎች ዘር ለመዘራት የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ • የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን • የዲጋፌ መስኖ የዝናብ ውሃ ማሰባባሰብ • በሰብል ማሳ የውሃ መከተር ማከናወን
በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑ ዞኖች				
ቦረና፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ አርሲ፣ የምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፣ ኮሬ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሌ፣ ባስኬቶ፣ አሪ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ እና ጃራር ዶሎ ዞኖች	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት	• ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገት • ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት • የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም	• ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት • የአፈር መሸርሸር	• ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች ላይ የእርጥበት መብዛት እና ውሃ በሰብሎች ላይ መተኛትን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ይህንን ለመከላከል የሚያስችሉ የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራትና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን በማዘጋጀት የቅድመ ጥንቃቄ ስራ መስራት • ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ ዝርያዎችን ከወዲሁ ማዘጋጀት • የአፈርና የውሃ እቀባ ለማከናወን የእርከን ስራ መስራት

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1.7 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሜይ የመጀመሪያ አስር ቀናት የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሃገራችን ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ያገኛሉ። ይህም የእርጥበት ሁኔታ የገጸ ምድር የውኃ ሃብትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ በኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በዋቢ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች እንዲሁም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑና በአግባቡ የውሃ ማፋሰሻ ቦዮች በሌላቸው ከተሞች አካባቢ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ይችላል፡፡ በመሆኑም ሊኖር የሚችለው ተፅዕኖ ለመከላከልና ለመቀነስ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ እንዲሁም የበልግ እርጥበት ማብቂያ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የክረምት ተጠቃሚ ባልሆኑ ተፋሰሶች እርጥበት አጠር በሆኑ ቦታዎች የሚገኘውን እርጥበት በተገቢው ሁኔታ በማከማቸት በውሃ እጥረት የሚከሰቱ ተፅዕኖዎች መቀነስ ያስፈልጋል፡፡

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ

የውኃ ተፋሰሶች	የሚጠበቀው የእርጥበት	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
በአብዛኛው ገናሌ ዳዋ ፣ የመካከለኛው እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ እንዲሁም የላይኛው እና የመካከለኛ ዋቢ ሸበሌ፣ እና የላይኛው አዋሽ ተፋሰሶች	ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት	• የመስኖ እና የሀይል ማመንጫ ግድቦች የውኃ ክምችት ማሻሻል • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ማሻሻል	• ቅፅበታዊ ጎረፍ የማስከተል እድል ይኖረዋል • የውሃ በጎርፍ መበከል • የውኃ ወለድ በሽታዎች ስጋት መጨመር • የጭቃ መንገዶች ላይ አነስተኛ ተፅዕኖ ማሳደር • አነስተኛ የውሃ ጉድጎድ በደለል መዝጋት • በከተሞች የትራፊክ መጨናነቅ	• የፍሳሽ መውረጃ ቦዮችን ማፅዳት • ደረቅ ቆሻሻን በተገቢው ሁኔታ ማስወገድ • የጎርፍ መውረጃዎች ወደ ነባር ፍሰታቸው መቀልበስ • የመጠጥ ውኃን አክሞ መጠቀም • በወንዝ ዳርቻ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መስጠት ወይም ማስተጠንቀቅ • ትንበያዎችን በቅርበት በመከታተል
በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው አባይ	ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ እርጥበት	• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል	•የመጠጥ ውኃ አቅርቦት በቂ አለመሆን •ከፍተኛ ትነት	• የዝናብን ውኃ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ማሰባሰብ • የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል ማስተዳደር • የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም • ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ተግባራትን ማከናወን
በአይሻ፣ አፋር ደናከል፣ መረብ ጋሽ እና በታችኛው አባይ እና ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች	ደረቅ ሁኔታ	የወራጅ ዉሃ በተለያዩ ፍሳሾች እንዳይበከል መከላከል	• የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት መቀነስ • የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የዉሃ መጠን መቀነስ • በቂ የውሃ ክምችት በሌለበት አካባቢ በተለይም አርብቶ አደር አካባቢዎች በእንስሳት የመጠጥ ውሃ ግጭት/አለመገባባትን ማስከተል	• የነበረውን ዉሃን በአግባቡ መጠቀም • የታቆሩ እና የጉድጓድ ዉሃን አክሞ መጠቀም

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et